የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 50
Addis Ababa 23th October, 2021


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻፴፯/፪ሺ፲፬**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**

**የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ማሻሻያ ደንብ**

**ገፅ............................................ ፪ሺ፯፻፳**


**Content**


**Regulation Number 137/2022**

**The Addis Ababa city government the community-based health insurance amendment Regulation**

**page............................................ 2720**


## ደንብ ቁጥር ፻፴፯/፪ሺ፲፬

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ማሻሻያ ደንብ

የውጪ ምንዛሬ ተመን ለውጥ በመኖሩ፣ በመድሃኒት እና ህክምና ግብዓቶች ዋጋ ላይ ከፍተኛ ለውጥ በመኖሩ፣ የጤና ተቋማቶች የዋጋ ክለሳ በማድረጋቸው ምክንያት የወጪ ለውጥ በመኖሩ፣ በከፍተኛ ሁኔታ የማህበረሰቡ የጤና አጠቃቀም እድገት በመፈጠሩ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ ዓ.ም አንቀፅ ፺፪ መሠረት ይህን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

## Regulation Number 137/2022

## The Addis Ababa city government the community-based health insurance amendment Regulation

**WHEREAS,** There has been changes in foreign exchange rates, significant changes in the prices of drugs and medical supplies, changes in costs due to health institutions revising prices, and a significant increase in the use of health care by the community;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 92 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this amendment Regulation.


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ፩. <u>አጭር ርእስ</u>

ይህ ደንብ “የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ደንብ ቁጥር ፻፴፯/፪ሺ፲፬” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. **"ደንብ”** ማለት የተሻሻለው የአዲስ አበባ አስተዳደር የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ደንብ ቁጥር ፹፮/፪ሺ፱ ነው፤
2. በደንቡ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በዚህ ደንብ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

## ፫. <u>ማሻሻያ</u>

የአዲስ አበባ አስተዳደር የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ደንብ ቁጥር ፹፮/፪ሺ፱ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. በደንቡ አንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀፅ (፪) ውስጥ “ነገር ግን ዓመታዊ መዋጮ በአባወራ ወይም እማወራ ከብር ፫፻፶ ያነሰ መሆን የለበትም” የሚለው ዐረፍተ ነገር ተሰርዞ “ነገር ግን ዓመታዊ መዋጮ በአባወራ ወይም እማወራ ከብር ፩ሺ ያነሰ መሆን የለበትም” በሚል ዐረፍተ ነገር ተተክቷል፤

## 1. <u>Short Title</u>

This regulation may be cited as “The Addis Ababa city government the community-based health insurance amendment Regulation No 137/2021”.

## 2. <u>Definition</u>

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **“Regulation”** means the Addis Ababa city government the community-based health insurance regulation No. 86/2017;
2. The words and phrases defined in the Regulation shall also be applied in this Proclamation.

## 3. <u>Amendment</u>

The Addis Ababa city Government the community-based health insurance regulation No. 86/2017 is hereby amended as follows:

1. Sub-Article (2) of Article 6 of the Regulation “However, the Annual contribution fee should not be less than birr 350.00 per head of the family” is deleted and replaced by “However, the Annual contribution fee should not be less than birr 1000.00 per head of the family”;

፪. በደንቡ አንቀፅ ፮ ከንዑስ አንቀፅ (፱) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፲) ተጨምሯል፤

"፲. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመዋጮው ሃምሳ በመቶ (፶%) በአስተዳደሩ የሚሸፈን ሲሆን ቀሪው ሃምሳ በመቶ (፶%) ደግሞ በአባላቱ የሚሸፈን ይሆናል ፡፡"

፬. **<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ ከጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

2. The following new sub Article (10) is added following sub Article (9) of Article 6 of the Regulation:

"10. Without prejudice to sub-article (2) of this article 50 percent of the annual contribution fee shall be paid by the member while 50 percent shall be paid by the City Administration";

4. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force as of the October 23, 2021.

**Done at Addis Ababa, this October 23, 2021.**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**